# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 156 ግንቦት 4 2003 ገጽ 1

**መለስ ዜናዊ "የመረጃ አውታሮችን በሙሉ ከተቆጣጠርኩ እና እውነትን የሚዘግቡ ጋዜጠኞች እንዳይኖሩ ካደረግሁ ህዝቡ እኔ የማወራውን ውሸት አምኖ ይቀበላል፤ ፀጥ ብሎም ይገዛልኛል" ብሎ ያምናል። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እነዚህን የመለስ ዜናዊን የትዕቢት እሳቤዎችን ዋጋ ማሳጣት ከቀዳሚ ተግባሮቻችን አንዱ ነው ብሎ ያምናል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ባሌቤት አዘብ መስፍን በእህቷ ልጅ ስም በአገሪቱ ለሚሰሩ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ብቸኛ ስምንቶ አቅራቢ በመሆን ብዙ ሚሊዮን ብር ትርፍ እያጋበሰች መሆኑ ተጋለጠ

በግልገል ጊቤ ቁጥር ሁለትና ሶስት እንዲሁም የሚሊየኒየሙ ፕሮጀክት እየተባለ ለሚዘፈንለት ግድብ ግንባታ የስራ ሂደት ዉስጥ የዘረኛውና የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ባለቤት የአዜብ መስፍን ቀጥተኛ የሙስና እጅ እንዳለበት ላለፉት 6 ወራት ከፍተኛ ክትትል ሲያደርጉ የነበሩ ምንጮች ማረጋገጣቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ። ኢሳት ባሳለፍነዉ ሳምንት እንደዘገበዉ "የሙስና ንግስት" በመባል የምትታወቀዉ የአዘብ መስፍን የሙስና ሰንሰለት በግንባታ ስራዎች፤ በማእድን አቅርቦትና በሌሎችም የተለያዩ ዘርፎች በስፋት የተንሰራፋ ሲሆን ይህንን የሙስና ሰንሰለት የአዘብ ቀኝ እጅ በመሆን በተግባር እየተገበረች የምትገኘዉ አቲኮ ስዩም አምባየ በሚል ስም በምትታወቀዉ የአዜብ መስፍን የእህት ልጅ እንደሆነች ታውቋል። ወ/ሮ አቲኮ ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ይህ ነዉ የሚባል ኃብት እንዳልነበራት ታሪኳን ያጠኑ የኢሳት ዘጋቢዎች ያረጋገጡ ሲሆን ባለፉት 20 አመታት ግን በእህቷና በእህቷ ባል ልዩ ትዕዛዝ "ወርኪድስ" ቢዝነስ ግሩፕ የሚባል ድርጅት ተከፍቶላት ሆን ተብሎ አያሌ የግንባታ ጨረታዎችን አንድታሸንፍ በመደረጉ የናጠጠች ቱጃር ሆናለች። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት 32 በመቶ ደረሰ፣ ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ የሁለት አሃዝ እድገት ውሸትነት በድጋሚ ተረጋገጠ

ላለፉት ሰባት አመታት የሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት እንዳስመዘገበ፣ በአምስት አመቱ የልማትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተብየው ደግሞ ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ተርታ እያሰለፋት እንደሆነ፣ በቅርቡ ደግሞ የሚለኒየም ግድብ የተሠኘ የውሸት ፕሮጀክት ነጠላ ዜማ ይፋ ያደረገው የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄደውን የዋጋ ግሽበት መቋቋም ተስኖት፣ በሃገሪቱ ያለው አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት በራሱ በወያኔ አፍ 32 በመቶ መድረሱ መታወቁን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ፡፡ እንደ ሪፖርተራችን ዘገባ የዋጋ ግሽበቱ በአንድ ወር ጊዜ ብቻ የሰባት በመቶ ጭማሪ አሳይቶአል::

ይህንን የዋጋ ግሽበት ተከትሎ የዘረኛውና አምባገነኑ አገዛዝ እንደ ግል ሃብቱ ተቆጣጥሮ ውሸት በሚያሰራጭባቸው የዜና አውታሮቹ፣ ቀደም ብሎ በሃገሪቱ በተከታታይ እየታየ ያለው የዋጋ ንረት የተከሰተው ስግብግብ ነጋዴዎች እቃዎችን ስለሚያከማቹና ተገቢ ያልሆነ ዋጋ ስለሚጠይቁ ነው በማለት የዋጋ ተመን ማውጣቱና በርካታ ነጋዴዎችን ወደ እስር ቤት ማጎሩ የሚታወቅ ነው። ይሁን እንጂ የፖለቲካ ትርፍ እስካስገኘ ድረስ አንድን ጥፋት በባሰ ሌላ ጥፋት ማድበስበስ ልማዱ የሆነው የዘረኛው መለስ ዜናዊና የባሌቤቱ አዜብ መስፍን አገዛዝ፣ የዋጋ ማስተካከያ አድርጊያለሁና ከእንግዲህ ወዲያ የኑሮ ውድነት ላሳር ነው በማለት በሚቆጣጠራቸው መገናኛ ብዙሃን ለአንድ ወር ያህል ህዝብ እንዳላደናቆረ በፍጆታ ዕቃዎች ጨርሶውኑ ከገቢያ መጥፋት ባዶነቱ እንደተጋለጠና እርቃኑን እንደቀረ የአደባባይ ምስጥር ሆኖአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አዲስ አበባ ከተማ በትራንስፖርት እጥረት እየተጨናነቀች ነው፣ ነዋሪዎች ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ አዲስ የሃሳብ አቅጣጫ ማስቀየሪያ ስልቱ ነው አሉ

በአዲስ አበባ ከተማ ሚኒባስ ታክሲዎች በሚያስከፍሉት ታሪፍ ላይ ጭማሪ እንዲደረግና ትናንሽ ታክሲዎች ደግሞ በርቀት መለኪያ እየተጠቀሙ ክፍያ የሚጠይቁበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መታቀዱን፣ የአገዛዙ ሹመኞች መግለጻቸውን ተከትሎ፣ በትናንትናው እለት በአዲስ አበባ ሁሉም ክፍለ ከተሞች የታክሲና አውቶብስ ፌርማታዎች ነዋሪዎች እጅግ ሲጨናነቁ መታየታቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ::

እንደሪፖርተራችን ዘገባ በተለይም ሰፈሮቻቸው እጅግ ራቅ ያሉ ቦታዎች የሚገኙ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ለበርካታ ሰአታት በታክሲ እጦት ሲንገላቱ እንደነበር አቅም ያላቸው በእግር ጉዞ ወደየቤቶቻቸው መድረሳቸውን፣ አቅም የሌላቸው ደግሞ ባሉባቸው አካባቢዎች ከሚገኙ ዘመዶቻቸው ቤት ለማደር እንደተገደዱ ገልጹአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

## በኢንቨስትሜንት ስም የሚካሄደው የደን ጭፍጨፋ እጅግ አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱ ተዘገበ

በተፈጥሮ ደን ክምችታቸው በከፍተኛ ደረጃ የሚታወቁትና በኢንቨስትመንት ስም ለባለሃብቶች የተቸበቸቡት ሰፋፊ ቦታዎች፣ በባለሃብቶቹ እየተጨፈጨፉና ከሰል ለማምረትም እየተቃጠሉ እንደሆነ የቤሻንጉል ጉምዝ ክልል ምንጮቹን በመጥቀስ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ገለጸ።

በክልሉ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የደን ቃጠሎ እንደሚካሄድ፣ ለእርሻ ስራ ብለው የሄዱ ባለሀብቶችም ደኑን በማቃጠልና ከሰል በማክሰል ወደ ውጭ እንደሚልኩ፣ የመንግስት ባለስልጣናትም በጥቅም እየተደለሉ አገሩን እያወደሙ መሆኑን የአካባቢው ሰዎች ለሚመለከታቸው አካላት በተደጋጋሚ መናገራቸውን ዘጋቢያችን ከስፍራው ያገኛቸውን ምንጮች በመጥቀስ ገልጹአል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለግብርና ልማት መሬት የወሰዱ ኢንቨስተሮች የሚያካሂዱትን መጠነ ሰፊ የደን ምንጣሮና ቃጠሎ አቁመው መሬቱን በአግባቡ እንዲይዙ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ትዕዛዝ መስጠቱን ሪፖርተር የተባለው አፍቃሪ ህወሃት ጋዜጣን በመጥቀስ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘግቡአል።

የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሚሊየኖች የሚቆጠር የሃገሪቱን ለም መሬት በነጻ ሊባል በሚችል ደረጃ ለውጪ ሃገር ባለሃብቶች በማደል ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል። የአገራችንን ለም መሬት ለባዕዳን ተቀራማቾች አሳልፎ በመስጠት የወያኔ ጸረ አገር ፖሊሲ ውስጥ እጅግ የሚገርመውና የሚደንቀው በመሬት ጥበት ለዘመናት ተጨናንቆ እና ተጣቦ በሚኖረው የአማራ ክልል ከመንዝ ህዝብ ተነጥቆ ለውጪ ባለሃብት ተሰጠ የሚባለው መሬት ጉዳይ ነው። በጋምቤላ፤ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በውጪ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በቶሮንቶ የተሳካ ስብሰባ አካሄዱ

ባለፈዉ ቅዳሜ ሚያዚያ 29 ቀን 2003 ዓም ካናዳ ቶሮንቶ ዉስጥ ከተለያዩ ማህበረሰብ የተወጣጡ ኢትዮጵያዊያን አወያዮችና ተሳታፊዎች የተገኙበትበት የተሳካ የ"በቃ" ንቅናቄ ስብሰባ መካሄዱንና የስብሰባዉ ተሳታፊዎችና እንግዶቹ አብሮ መስራትንና ለአንድ ዓለማ በጋራ መታገልን የሚያሳይ የአቋም መግለጫ ማውጣታቸውን ቶሮንቶ ዉስጥ የሚገኘዉ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው ባስተላለፈልን ሪፖርት ገልጿል።

በእለቱ ስብሰባ በመቶዎች የሚቆጠሩ የኦጋዴን፤ የአፋርና የኦሮሞ ብሄረሰብ አባላት እንዲሁም ሌሎች ኢትዮጵያዊያን የተገኙ ሲሆን፡ በጋራ ያወጡትም መግለጫ "ኢትዮጵያ አንድ ናት"፡ "አንድነታችን በተለያዩ ማህበረሰቦች የተገነባ አንድነት ነው፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሁሉም ነገር በፊት የሰውነትና የተፈጥሮ ነጻነታችንና መብታችን መከበር ከምንም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ነው" የሚል እንደነበረ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ካስተላለፈልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል።

በእለቱ ስብሰባ በመጀመሪያ የተናገሩት፡ ከአፋር ብሄረሰብ የተወከሉት አቶ አሎ አይደሂስ ሲሆኑ እሳቸዉም- "ሕወሀት/ኢህአዴግ በማሳ ውስጥ እንደበቀለና፡ እህል እንደሚያቀጭጭ አላስፈላጊ ዛፍ ከመሰሉት በኋላ፤ አንድ ላይ አይቀመጡም፡ አይወያዩም፡ ብለዉ ለያይተዉ የሚያዩን ተቃዋሚዎች ዛሬ መሰባሰባችን እጅግ አስደንግጧቸዋል ካሉ በኋላ ይህ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የዘረኛውን መለስ ዜናዊ አገዛዝ የመሬት ቅሚያ ፖሊሲ በመቃወም የሰሜን ጎንደር የደባርቅ ወረዳ ህዝብ ተቃውሞ አስነሳ በወረዳ የተነሳው ቅዋሜ እስካሁን አልበረደም

ሰሞኑን ከወደ ኢትዮጵያ የሚሰማዉ ዜና "ወያኔ መሬት ቀማ" ወይም "ወያኔ ቤት አፈረሰ" የሚል ብቻ ሆኗል፡፡ መቀሌ ዉስጥ የህዝብ ቤት ካላፈረስኩ ብሎ ከከተማዉ ነዋሪዎች ጋር ግብግብ ዉስጥ ገብቶ የከረመዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፊቱን ወደ ጎንደር አዞሮ_ሰሜን ጎንደር ዉስጥ በደባርቅ ወራዳ የምንቃር ንኡስ ከተማ ህዝብ ለግጦሽ የሚጠቀምበትን ሰፊ መሬት ለባለሃብቶች ለመሸጥ ሲያስማማ የአካባባዉ ህዝብ በከፍተኛ ቁጣ ተንቀሳቅሶ መሬቴን አላስነካም ብሎ የወያኔን ባለስልጣኖች አሳፍሮ ወደመጡበት መልሷቸዋል።

ጀግናዉ የደባርቅ ከተማ ህዝብ የወያኔን ተንኮል ተከታትሎ ማክሸፍ የቻለዉ የክልሉ ባለስልጣናት ለአካባቢው ህዝብ የአትሌቲክስ መንደር እንሰራለን በሚል ሽንገላ መሬቱን ለመከለልና የመሰረት ድንጋይ ለማኖር ወዳካባቢው እንደሚመጡ አስቀድሞ መረጃ ከደረሰው በኋላ ውስጥ ለውስጥ ሲመካከርና ሲዘጋጅ ከቆየ ቦኋላ እንደሆነ ታውቆአል። ህዝብ ይቃወመናል የሚል ምንም አይነት ስጋት ያልነበራቸው የክልሉ የወያኔ ሹመኞች በቦታው እንደደረሱ በነቂስ ወጥቶ በስፍራው ይጠባበቃቸው የነበረውን ህዝብ እንደለመዱት በጸጥታ ሃይል ለመበተን ጥረት ያደረጉ ቢሆንም መሬቴን አላስነካም ብሎ በብሶትና በቁጣ ገንፍሎ የወጣዉን ህዝብ መቆጣጠር ተስኗቸዉ ፊታቸዉን በሀፍረት ሸፍነዉ ወደመጡበት ለመመለስ ተገድደዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የመለስ ዜናዊን የመረጃ አፈናን በህዝባዊ ኃይል እንበጣጥሳለን!

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአገር ውስጥ የሚገኙ የመረጃ መረቦችን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር፤ ከውጭ አገራት የሚተላለፉ የሬድዮና የቴሌቪዥን ሞገዶችን በይፋ በማፈን ኢትዮጵያ አገራችን በመረጃ ከዓለም የተነጠለች ደሴት ለማድረግ ተግቶ ይሠራል፤ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብም ያወጣል። በሌላ በኩል ደግሞ ለሙያቸው ክብር ያላቸው ጋዜጠኞችን በክሶች ብዛት፤ በእስርና እንግልት እንዲሁም ከአቅማቸው በላይ በሆነ የገንዘብ ቅጣት እንዲሸማቀቁ በማድረግ እውነት ዘጋቢ ስታጣ የኢትዮጵያ የመረጃ አየር በውሸት የተሞላ እንዲሆን አድርጎታል።

መለስ ዜናዊ "የመረጃ አውታሮችን በሙሉ ከተቆጣጠርኩ እና እውነትን የሚዘግቡ ጋዜጠኞች እንዳይኖሩ ካደረግሁ ህዝቡ እኔ የማወራውን ውሸት አምኖ ይቀበላል፤ ፀጥ ብሎም ይገዛልኛል" ብሎ ያምናል። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እነዚህን የመለስ ዜናዊን የትዕቢት እሳቤዎችን ዋጋ ማሳጣት ከቀዳሚ ተግባሮቻችን አንዱ ነው ብሎ ያምናል።

በአገራችን ውስጥ አዎንታዊና ዘላቂ ለውጥ እንዲመጣ የምንፈልግ ወገኖች በሙሉ ከዚህ በታች ለተመለከቱት ሁለት ጉዳዮች ትኩረት መስጠት ይኖርብናል ብሎ ግንቦት 7 ያምናል።

1. በመለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ የግንቦት 7 ሬድዮና ሌሎችም አገር ወዳድ የአጫጭር ሞገድ ስርጭቶች በተከታታይ ያፍናል። የአሜሪካና የጀርመን ድምጽ ሬድዮዎች እንደወቅቱ አሳሳቢነት ይታፈናሉ። የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ስርጭትን ለማፈን በራሱ በመለስ ዜናዊ የሚመራ ኮሚቴ ተቋቁሟል። በግብፅ ህዝባዊ አብዮት ወቅት አልጀዚራም ታፍኖ ነበር። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሚዲያን ለመቆጣጠር ምን ያህል የተቀነባበረ ሥራ እየሰራ እንደሆነ ነው። ለዚህ የሚኖረን አፀፋዊ ምላሽ ምንድነው? በአገራችን ውስጥ ህዝባዊ አብዮት ሲነሳ የምጠቀመው የመረጃ መረብ ምንድነው?
2. ጋዜጠኞች በሚደርስባው ተከታታይ ወከባ፣ እስርና ቅጣት ምክንያት ሥራቸውን በነፃነት መከወን አልቻሉም። እውነት ተናግሮ ከመሰቃየት "ዋሽቶ ማደርን" የሚመርጡ የስም ጋዜጠኞች ቁጥር እየበረከተ ነው። ለእውነቱ የቆሙ ፕሮፌሽናል ጋዜጠኞች ቁጥር በየእለቱ እየተመናመነ ነው። አሁን በአገር ውስጥ ያሉት ሃቀኛ ጋዜጠኞችም በአገዛዙ ዓይን ውስጥ በመሆናቸው መታዘብና መዘገብ የሚችሉት ነገር እጅግ ውስን ነው። ይህንን አሳሳቢ የሆነውን የጋዜጠኛ እጥረትን በምን እንከላከላለን? ህዝባዊው አመጽ ሲነሳ ሁኔታውን ተከታትለው ለኢትዮጵያም ለዓለምም የሚዘግቡልን ጋዜጠኞችን ከየት እናገኛለን?

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከላይ የተመለከቱት ሁለት ጥያቄዎችን አንስቶ ሲመክርባቸውና መፍትሄዎችንም ሲያፈላልግ ቆይቷል። ንቅናቄያችን እነዚህ ጥያቄዎች ነፃነታችንና አገራችን የምንወድ ወገኖችን ሁሉ ሊያሳስቡ የሚገቡ ናቸው ብሎ ያምናል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ምንም እንኳን ችግሮቹ ውስብስብ ቢሆኑም በደንብ ከታሰበባቸው እና ጥረቶቻችንን ማስተባበር ከቻልን የመለስ አገዛዝን የመረጃ አፈና መበጣጠስ እንችላለን ብሎ ያምናል። ችግሮቹ ዝርዝር ጥናት የሚፈልጉ ቢሆንም ለሁለቱ ዓበይት ችግሮች የሚከተሉት ሁለት አጠቃላይ መፍትሄዎች መስጠት ይቻላል ብሎ ግንቦት 7 ያምናል።

1. የሚዲያ አውታሮች ታፍነዋል ብለን ተስፋ ቆርጠን አናውቅም፤ ወደፊትም የትኛውም የአፈና መጠን ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም። የመለስ አፈና በጠነከረ መጠን ምላሻችን እየባሰ መምጣት ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ ሁላችንም በጋራ መቆም ይኖርብናል። በየጊዜው ለአፈና የማይመቹ ስርጭቶችን መጀመር እና አገዛዙ ሊቆጣጠራቸው የማይችሉ የመረጃ ልውውጥ ዘዴዎችን በሥራ ላይ ማዋል ይገባናል። ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከመጠቀም አንስቶ ከሰው-ወደ-ሰው ወደሚተላለፍ ባህላዊ የመረጃ ቅብብሎሽ ድረስ ያሉትን አማራጮች በሙሉ ለመጠቀም ዝግጁዎች ነን። በደንብ ከታሰበበትና በሚገባ ከተደራጀን የመለስ አገዛዝን የመረጃ አፈና መበጣጠስ የሚቻልባቸው መንገዶች ብዙ ናቸው።
2. ፕሮፌሽናል ጋዜጠኞችን በማሰርና በማዋከብ የተፈጠረን ክፍተት በህዝባዊ ጋዜጠኝነት መሙላት ይኖርብናል። ከእንግዲህ እያንዳንዱ ዜጋ ራሱን እንደ ጋዜጠኛ መቁጠር ይኖርበታል። ዜጎች እጃቸው ውስጥ የገቡ መረጃዎችን ለእውነት ወደ ቆሙ የሚዲያ አካላት እና/ወይም ወደ ኢንተርኔት ብሎጎች፣ ዩ ቱብ፣ ፌስ ቡክ እና መሰል አውታሮች ወዲያውኑ የሚያስተላልፉበት መንገድ ሊመቻች ይገባል። ኢትዮጵያዊውን ወገናችንን ሁሉ ጋዜጠኛ ካደረግነው ከኛ የሚያመልጥ ዜና እንዳይኖር ማድረግ እንችላለን። አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን አቅም በፈቀደ መጠን የጋዜጠኛ መሠረታዊ መገልገያዎች - ለምሳሌ፡ እስክሪብቶና ወረቀት፣ ካሜራና የድምጽ መቅረጫ እንዲይዙ እናሳስባለን። በኪሳችን ይዘን የምንዞረው ተንቀሳቃሽ ስልካችንን ለድምጽና ምስል መቅረጫነት መገልገል ይኖርብናል። ምስሎችንና ድምፆችን ከተንቀሳቃሽ ስልካችን ወደ ኢንተርኔት ወይም ኢሜል ማስተላለፊያ ገመዶች ከኪሳችን መጥፋት የለባቸውም። መልዕክቶች ከተላለፉ በኋላ የስልካችንን ቀፎ የማጽዳት ልማድንም ማዳበር ይኖርብናል። ህዝባዊ ጋዜጠኝነት የራሱ ድክመቶች የሉትም ማለት አይደለም። ፕሮፌሽናል ጋዜጠኝነት የሚፈለግባቸው በርካታ ጊዜዓት እንዳሉ ምንም ጥርጥር የለውም። በቅርቡ እንገባበታለን ለምለው ህዝባዊ አብዮት ግን ፕሮፌሽናል ጋዜጠኝነት በህዝባዊ ጋዜጠኝነት ካልታገዘ ወቅቱ የሚፈልገውን አገልግሎት መስጠት አይችልም።

መለስ የሚዲያ አውታሮችን በመቆጣጠርና በማፈን፤ ጋዜጠኞችን በማዋከብ ኢትዮጵያን ከዓለም እይታ ሊያርቃት ቆርጦ ተነስቷል። እኛ ደግሞ መለስ ፈጽሞ ባላሰበውና ሊቆጣጠረው በማይችለው መንገድ መጥተንበታል። ከባህላዊ እስከ ዘመናዊ የዜና አውታሮች ድረስ ያሉትን አማራጮችን እንጠቀማለን። ከአሁን ጀምሮ ነፃነት የጠማው የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ ጋዜጠኛ ነው። አንዳችም ነገር ከእይታና ከዘገባ አያመልጥም።

**መሮናል!!! የመለስ ዜናዊ አፈና በጭራሽ አያቆመንም። "የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቃ!" ብለናል።**

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጉደስ!!!**

### የዘረኛው መለስ ዜናዊ ባሌቤት አዘብ መስፍን በእህቷ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በርካታ ኢትዮጵያዊያን ግለሰቧ ከኢህአዴግ አባላትና ከአዜብ መስፍን ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላት ያዉቃሉ ሆኖም የአዘብ መስፍን የስጋ ዘመድ መሆኗ እንዳይታወቅ ብርቱ ጥንቃቄ ሲደረግ እንደቆየ ለማወቅ ተችሏል። የወያኔን በሥልጣን ላይ መፈናጠጥ ተከትሎ በአቋራጭ ከከበሩት የዘመኑ ቱጃሮች አንዷ የሆነችው አቲኮ ስዩምን በቅርብ አውቃታለሁ የሚሉ አንድ አዛዉንት ወ/ሮ አቲኮ በትውልድ ኤርትራዊ በመሆኗ ከአዜብ መስፍን ጋር የንግድ እንጅ የስጋ ዝምድና የላትም ብለዉ መከራከራቸው የተገለጸ ቢሆንም ግለሰቧ በእናቷ የወልቃይት ተወላጅ የአዜብ መስፍን እህት ልጅ መሆኗ ተረጋግጧል። ኤርትራዊነቷ እየተጋነነ የሚወራዉ ከአዘብ መስፍን ጋር ያለቻዉን የስጋ ዝምድና ህብረተሰቡ እንዳያዉቀዉ ሆን ተብሎ የሚነገር የማሳሳቻ ወሬ ነዉ።የአዜብ መስፍን የእህት ልጅ የሆነቺው ወ/ሮ አቲኮ ስዩም በ1992 ዓም የነበራት ንብረት ቢኖር አንድ "ፒካፕ" የኪራይ መኪና ብቻ ሲሆን፣ ዛሬ ግን በብዙ መቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ካፒታል በስሟ እያንቀሳቀሰች መሆኑ ታውቋል።

የአቲኮ አምባዬ ንብረት የሆነው ወርኪድ ቢዝነስ ግሩፕ የህዳሴዉን ግድብ ፕሮጀክት ኮንትራት አሸነፈ ለተባለው ለሳሊኒ ኩባንያ ዋነኛዉ የሲሚንቶ የአሸዋና የተለያዩ እቃዎችን አቅራቢ በመሆን መመረጡ የታወቀ ሲሆን፣ ይሄው ኩባንያ ለግልገል ጊቤ ቁጥር አንድ፣ ቁጥር ሁለትና ለሌሎችም ሶስት የሀይል ማመንጫ ግንባታዎች ስሚንቶ ሲያቀርብ መቆየቱ የሚታወስ ነዉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዜና አዜብ መስፍን በእህቷ ልጅ ስም የምታንቀሳቅሰው ወርኪድ ቢስነስ ግሩፕ የሚባለዉ ኩባንያ በርካታ ንብረት እንዳለው ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ፤ በግንባታ ስራ ላይ የተሰማሩ ከ 80 በላይ ዩሮ ትራክር፣ ከ10 በላይ እቃጫኝ ሎቤድ መኪናዎች፣ ከ100 በላይ ገልባጭ መኪናዎችና፣ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ስካቬተሮች፣ ግሬደሮች፣ ዶዘሮችና የተለያዩ ማሽኖች በስሙ በማንቀሳቀስ ላይ መሆኑኑ ተገልጿል ።አዜብ መስፍን በአቲኮ ኩባንያ ስም የዳሎል ማእድን ማውጫን የምትቆጣጠር ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ አዜብ መስፍን አዲስ አበባ ዉስጥ የስፖርት ቤቶችን ጨምሮ በርካታ ለቁጥር የሚታክቱ ድርጅቶች እንደሏት ታውቋል::

### በኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት 32 በመቶ ደረሰ፣ የወያኔ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶር ብርሃኑ ነጋን ጨምሮ በርካታ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ኢኮኖሚው ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ገንዘብ በማተም እድገት እንደተገኘ ለማስመሰል ያደረገው ጥረት የዋጋ ንረቱንና የገንዘብ ግሽበትን እንዳስከተለ በተደጋጋሚ መግለጻቸው አይዘነጋም:: ባለሙያዎቹ ዘረኛው አገዛዝ ያወጣው የዋጋ ቁጥጥር ተመን ሊሰራ እንደማይችል እንዲያውም ችግሩን ይበልጥ ለማባባስ የእቃዎችን አቅርቦት እጅግ ሊቀንሰው እንደሚችል አስቀድሞው ተንብየው እንደነበረና በገሃዱ አለም እየሆነ ያለውም ይሄው ሃቅ መሆኑ እየታየ ነው።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በርካታ ከተሞች ስኳርና ዘይትን ጨምሮ በርካታ የፍጆታ እቃዎች ከገበያ ላይ በመጥፋታቸው የተነሳ አገዛዙ በማከፋፈሉ ሥራ ውስጥ እንደገባና ተጨማሪ የፖለቲካ ድጋፍ ማግኛ ምንጭ እያደረገው እንዳለ፤ በስርጭቱ ላይ አገዛዙን ለሚደግፉ ሰዎች እየተደረገ ያለው መድልዎ ማሳየቱን ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው ግለሰቦች አረጋግጠዋል።

### የዘረኛውን መለስ ዜናዊ አገዛዝ የመሬት ቅሚያ ፖሊሲ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

"ላለፉት 20 አመታት ያታለላችሁንና ከአብራካችን የወጡ የራሳችንን ልጆች እንደመሳሪያ በመጠቀም ያዋረዳችሁን ይበቃል ከአሁን ቦኋላ በምንም አይነት መንገድ አንታለልላችሁም" ያለው የደባርቅ ነዋሪ "እስከዛሬ ተታልለን ብዙ ነገር ሰጥተናችኋል ካሁን በኋላ ግን የምንሰጣቸሁ ምንም ነገር የለም። ደግሞስ እንዴት ብትንቁን ነዉ በስፖርት ስም መሬታችንን ለውጭ ባለሀብቶች ልትሰጡብን የመጣችሁት" ሲል የደባርቅ ህዝብ ቁጣዉን በምሬት ሲገልጽ የዋለ ሲሆን፣ የህዝቡን ቁጣ መቋቋም የተሳናቸው የወያኔ መልዕክተኞች ለቴሌቪዥን ፍጆታ እንዲሆናቸዉ በዕቅድ ያልተያዘ ቦታ ላይ የመሰረት ድንጋይ አስቀምጠዉ በሀፍረት ወደመጡበት ተመልሰዋል።

ጸጥታ እንዲያስከብር ወደ አካባቢወ_ተጠርቶ የመጣው የጸጥታ ሃይል ከአንዳንድ ተቃዋሚዎች ጋር ግጭት ለመፍጠርና ድብደባ ለማካሄድ ሙከራ ከማድረጉም በላይ የታጠቀዉን መሳሪያ ወደሰማይ ሲተኩስ እንደነበር በአካባቢዉ የነበሩ የአይን ምስክሮች ተናግረዋል። ደባርቅ ዉስጥ በመሬት ጉዳይ የተቀሰቀሰው ተቃውሞ አሁንም እንዳልበረደና ህዝቡ መሬቱ እንዳይሸጥበት በንቃት አካባቢዉን እየጠበቀ እንደሆነ ተገልጿል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

## የዴሞክራሲ ትግሉ በኢትዮጵያ: የማጥቃት ስልቶቻችን

### ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በአትላንታ በተካሄደ ህዝባዊ ስብሰባ ያደረጉት ንግግር አፕሬል 23 2011 (ክፍል 3 - የመጨረሻ ክፍል)

የኣውራምባ ታይምሱ እውቅ ሀያሲ ኣቤ ቶክቻው የኣባዩን ግድብ ኣስመልክቶ የህዝቡን ስሜት በሁለት ጉዋደኛሞች ጭውውት ኣስመስሎ ሲገልጽ ኣንደኛው "ለኣባይ ግድብ ያሰብኩትን ብር በሙሉ ጠራርጎ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪው ሙልጭ ኣድርጎ ባዶዬን ኣስቀረኝ: ምናባቴ ይሻለኛል?...ለዚህ የነዳጅ ጭማሪ ጸረ_ኢትዮጵያ ሀይሎች በተለይም የሻእቢያ ነጭ ለባሾችን መጠርጠር የለብንም ትላላችሁ?" ሲለው ሌላኛው "ሀይል ለማያመነጩት ግድቦች የሚያወጡትን ገንዘብ ለሀይል ማመንጫው ቢያውሉት፤ እንኳን ኣባይንና ኣጠቃላይ ድህነታችንን መገደብ በተቻላቸው ነበር...ሀይል የማያወጡት ግድቦች ለመሆኑ እነማን ናቸው ስለው: ፈጠን ብሎ "እነ ኣሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ: እነ ጀርመን ሬዲዮ: እነ ኢሳት ቴሌቪዥን ኣለኝ: እሱን ወደ ግድቡ ያዙሩት: እኛ ችግር ጠብሰን ይበቃናል:: በመዋጮ ደግሞ መጠበስ የለብንም ኣለኝ::" ብሎ ነበር ባለፈው ሳምንት ኣምዱ የከተበው:: የቅዱስ ገብረኤል ኣንደኛና ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ለኣባይ ግድብ ገንዘብ ኣዋጡ ከምትሉን መጀመሪያ በህይወት ኣኑሩን ብለው ነው ገንዘብ ለመሰብሰብ የመጡ ካድሬዎችን ያባረሯቸው:: ስለ መለስ/ኢህኣዴግ "ሳይንሳዊና ልማታዊ" ኣመራር ሳይሆን የኣገሪቱ ወጣት "መለስ በቃ" እያለ ነው በየግድግዳው የሚጽፈው:: ከሰሞኑ ከኦሮሞ ወጣቶች: ከሚዛን ቴፒ: ሀዋሳ: ኣዲስ ኣበባ ዩኒቨርሲቲና ሌሎችም ቦታዎች የሚበተኑ ወረቀቶችም ሆኑ በፌስ ቡክና በቴክስት የሚራቡ መልእክቶች የሚጠቁሙት መቼ እንቅስቃሴው ይጀመራል የሚለውን እንጂ ኢህኣዴግ በኣስቂኝ መግለጫው (በኣይጋ ላይ ተመልከቱት) እንዳለው ስለ ድንቁ የመለስ/ኢህኣዴግ ሳይንሳዊ ኣመራር ኣይደለም::

የነመለስ የማስቀየሻ እንቅስቃሴ ሙሉ ለሙሉ ባፍጢሙ የተደፋው ግን ከኣይነደረቅነታቸው (ወይም ከጭንቀታቸው) የተነሳ ይህንን የማሳሳቻ ተልእኮ በጣም ብዙ ብር ኣውጥተው የውጭ ነዋሪውን ለማማለል በተላኩት የመለስ መልእክተኞች ፊት ነው:: የማስቀየሺያ እስትራቴጂው በነመለስ "ሳይንሳዊ" ስሌት ሁለት ከፍተኛ የፖለቲካ ግኝቶችንና ኣንድ የእግረ መንገድ የገንዘብ ትርፍ ያስገኛል ተብሎ የተሰላ ነበር: እነኝህም:-

1. በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ በተቻለ መጠን መከፋፈል (በዘር: በሀይማኖት: በፖለቲካ ኣመለካከት...ወዘተ)
2. በውጭ ያለውን የተቃዋሚ ሀይል ማዳከም: ይህንንም በመንደራችሁ መጥተን እንደፈለግን ፎልለን: በዳያስፖራው የልማት መንግስት ተብለን ኣስጨብጭበን: ኣውራ ተቃዋሚዎችን ለኣገር ልማት ያልቆሙ "ጽንፈኞች" ኣስብለን እንሄዳለን:: ከዚያ በኋላ እስከወዲያኛው ድረስ ተቃዋሚ ነኝ የሚል ኣይነሳም...ወዘተ
3. በዚህ ኣጋጣሚ "ከልማቱ ልጠቀም" የሚሉ ደካሞች (suckers) ኣይጠፉምና ከነሱ ደግሞ ትንሽ የቦንድ ገንዘብ በዶላር ከሰበሰብን "ዝበለጸ" ብለው ይመስላል መለስ ኣዜብና በረከት ከዳያስፖራ ኣማካሪዎቻቸው ጋር ያሰሉት::

የመለስ መንግስት ይህ ኣላማው በፍጹም ኣለመሳካቱ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ከታሰበው በተቃራኒው ውጤት ማስከተሉ ከላይ እንዳልኩት ይህ መንግስት ኣንድ ሀሙስ የቀረው መሆኑን እንድንገምት ያደርገናል:: እከፋፍላለሁ ብሎ መጥቶ እንዲያውም ዳያስፖራው ከዚህ በፊት ሆኖ በማያውቅ መልኩ በጎሪጥ ይተያዩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን "ኣሁንስ በዛ: በቃ_ጋዬ" ብለው ኦሮሞው፤ ኦጋዴኑ፤ ኣማራው፤ ጉራጌው፤ ጋምቤላው፤ ባጠቃላይ መላው ኢትዮጵያዊ በጋራ ተቃወማቸው:: ይህ ብቻ ኣይደለም:: በዚህ በዛሬው ስብሰባ እንደምታዩት ከኣንድ ጊዜ የተቃውሞ ሰልፍ ኣልፎ ትግሉን በጋራ ለማስኬድ የሚያስፈልገውን የመተሳሰብ፤ የመተማመን፤ በጋራ የመወያየትና የጋራ ራእይ የመቅረጽ እንቅስቃሴ በጥንካሬ ገፋበት::

ኣዳክሜ እሄዳለሁ ያለውን ዳያስፖራ እንዲያውም እልህ ውስጥ ከትቶት የበለጠ ኣጠናክሮት ኣረፈው:: በኣሜሪካን ኣገር በተለያዩ እስቴቶች እንዲሁም በኣውሮፓ በእንግሊዝና በፍራንክፈርት በተደረጉት ስብሰባዎች ሁሉ የተሳተፉ ወገኖች እንደገለጹት ምናልባት የቅንጅት ኣመራሮች ከታሰሩ ጊዜ ወዲህ ታይቶ የማይታወቅ የሰው ሀይልና እልህ የተቀላቀለበት ስሜት ነው ፈጥረው የሄዱት:: ለዚህም ነው ለነሱም የስትራቴጂው መባረቅ ኣስደንግጧቸው ወዲያውኑ ማስፈራራት ወደለመዱት የኢትዮጵያ ህዝብ ተመልሰው ልክ ድሮ ደርግ "የጨለቅለቅቱ ገበሬዎች የኣሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምን ኣስጠነቀቁ" ይል እንደነበረው ገበሬውና ተማሪው ዳያስፖራውን "በሰልፍ እንዲያወግዝ" በካድሬዎች መቀስቀስ የጀመሩት:: ምን ያህል ግራ እንደተጋቡ የሚያሳየው ግን ካድሬዎቹ ዳያስፖራውን ኣውግዙ እያሉ በራሳቸው የመገናኛ ብዙሀን ደግሞ በውጭ የተካሄደው ስብሰባ እንዴት የተሳካ እንደነበረና ዳያስፖራው ገንዘብ በገፍ ሊያዋጣ ቃል እንደገባ ለህዝቡ ያበስሩታል::

ሶስተኛው በቤታቸው ያራዳ ወይም የ "ወዲ ሹቅ" ስራ የነበረው በኣባይ ቦንድ ስም ዶላር የመሰብሰቡም ነገር ብዙ ኣላዋጣም:: እስካሁን ኣይደለም ብዙ ዶላር ሊሰበስቡ ለትርኢቱ ያወጡትን ቢያንስ ግማሽ ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ወጪ እንኳን ለማግኘት ኣልቻሉም:: ባጠቃላይ ትርኢቱ እንደቀሺም ዘፋኝ ኮንሰርት በባዶ ኣዳራሽ: የዘፋኙ የቅርብ ወዳጆች ብቻ በተገኙበት: በፍጹም ኪሳራ ተደመደመ:: ባጠቃላይ ከነመለስ የሰሞኑ መንቀዥቀዥም ሆነ ከህዝቡ ምላሽ መገንዘብ የሚቻለው ሁኔታው ለለውጥ የተዘጋጀ መሆኑን ነው:: ለውጥ ተጀመረ ማለት ግን ሙሉ ለሙሉ ወዲያውኑ ይሳካል ማለት ኣይደለም:: ለስኬቱ ኣስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ትግሉን በሚያካሂዱ ሀይሎች ዘንድ መፈጸም ያለባቸው ብዙ ስራዎች ኣሉ:: የዛሬ ንግግሬን ለመቋጨት ከነኝህ ኣስፈላጊ ነገሮች ውስጥ በጣም ወሳኝ በሆነው በዴሞክራሲ ሀይሎች መሀል በጋራ ሊኖር ስለሚገባው "የመዳረሻ ቦታ" (end game) ኣመለካከት ላይ ድረጅታችን ያለውን ኣቋም ውይይት ለመቆስቆሻ ያክል ላቅርብና ላብቃ::

### 4. ኣሁን ኣጥቂዎች እኛ ነን

የዚህ የመዳረሻ ቦታ ኣመለካከት ሁለት ገጽታዎች ይኖሩታል:: ኣንደኛው በስነልቦና ደረጃ የዴሞክራሲያዊው ሀይሎች ሊኖራቸው የሚገባው የመንፈስ ዝግጁነት ነው:: በዚህ ዙሪያ ከዚህ በፊት በኖርዌይ ንግግሬ እንደገለጽኩት ትግላችን እንደከዚህ በፊቱ ወያኔ የሚወረውረው ነገር ላይ የመከላከል እርምጃ መውሰድ ሳይሆን ቀጥታ የማጥቃት እርምጃ የሚወሰድበት ደረጃ ላይ መድረሳችንን መረዳት ነው:: ይህ ኣስፈላጊ የሆነ የስነልቦና ለውጥ ነው:: ኣሁን ተነሳሽነቱ (initiative) የኛ መሆኑን መቀበልና የምንወስደው እርምጃ ሁሉ ይህንን ከስሌት ያስገባ ማድረግ ያስፈልጋል:: ይህ ከተከላካይነት ወደ ኣጥቂነት የሚደረግ ሽግግር ደግሞ ከዚህ በፊት እንዳልኩት 1ኛ) ጠላትን መነጠልና፣ 2ኛ) ወዳጅን ማብዛት፣ ከያንዳንዱ እርምጃችን ጋር የተሳሰረ የሁልጊዜም ስሌታችን ኣካል ማድረግን ይጠይቅብናል::

ሁለተኛውና ወሳኙ ቁምነገር ደግሞ የዴሞክራሲ ሀይሉን በኣንድ የመታገያ ኣጀንዳ ዙሪያ ማሰለፍና ቆይቶም በዚህ መስመር ዙሪያ ላይ የታጠረ ህብረ ድርጅታዊ ኣመራር ስር ማሰባሰብ ነው:: ኣሁን ኣገራችን ባለችበት ሁኔታ ሁለቱም ጊዜ ሳይወስድ መፈጸም ያለባቸው ቢሆኑም የኋለኛው ትንሽ ጊዜ የሚወስድ ቢሆን እንኳን የመታገያ መስመሩን በተመለከተ ሁሉም በየድርጅቱ ኣሁኑኑ ሊያደርገው የሚችለው ነገር ስለሆነና ባጠቃላይ ህዝቡም ዘንድ መናበብን ማዳበር ስለሚገባ ኣሁኑኑ ማድረጉ ኣስፈላጊ ይመስለኛል:: በኣገራችን ይህንን የጋራ የመታገያ ኣጀንዳ ግን የግድ የፖለቲካ ድርጅቶች ማውጣት የለባቸውም:: እንደ ግብጽና ሌሎች የሰሜን ኣፍሪካ ኣብዮቶች ሁኔታውን እየኖሩበት ያሉትና ትግሉንም ከዳር የሚያደርሱት ወጣቶች የሚታያቸውን ማድመጥ: በጣም ኣስፈላጊ ነው::

በዚህ ረገድ የኦሮሞ ወጣቶች ማህበር የህዝብ ቁጣ ሊያነጣጥርባቸው የሚገቡ መሰረታዊ ነጥቦችን በቅርቡ ዘርዝሮ በጽሁፍ አውጥቷል። ይህ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ( Freedom, Liberty and democracy shall prevail! ) በሚል ርእስ በብሄራዊ ወጣቶች የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተዘጋጀ ሰነድ በውስጡ በርካታና በደንብ የታሰበባቸው የህዝባዊ እምቢተኛነቱ ትግል ሊያተኩርባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን አስቀምጧል። እያንዳንዱ ድርጅት፣ ቡድን ወይም ታጋይ የራሱን የመታገያ ነጥብ በየግሉ እያነሳ የመታገል መብት ያለው መሆኑ ቢታወቅም ትግሉን ለማቀላጥፍና በጋራ ስምምነት የተደረሰባቸን መሰረታዊ ጉዳዮች አስቀድሞ አውቆ መንቀሳቀስ ለውጤታማነቱ ኣስፈላጊ ነው። ይህን እውን ለማድረግ የኦሮሞ ወጣቶች ባቀረቡት ሰነድ ላይ የሰፈሩትን ህዝባዊ ጥያቄዎች የመታገያ አጀንዳዎች ተቀብሎ በእነዚህ ላይ የሚጨመር ካለ እንዲጨመር እያደረጉ መቀጠሉ የተሻለ ውጤት ያስገኛል ብሎ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ያምናል። ሌሎችም ድርጅቶች: ቡድኖችና ታጋዮች ይህ የኦሮሞ ወጣቶችን የመታገያ ሰነድ እንደሚቀበሉት በመግለጽ የቀረበው ጥያቄና የመታገያ አጀንዳ የመላ ሃገሪቱ ህዝብ የወጣቱና የአረጋዊው፣ የሴቱና የወንዱ፣ የክርስቲያኑና የሙስሊሙ እንደሆነ በማያሻማ ቋንቋ መግለጽ ትግሉን ወደፊት ያራምደዋል የሚል እምነት ንቅናቄያችን አለው። ከዚህ በመነሳት የሚከተሉትን በኦሮም ወጣቶች መግለጫ ላይ የተወሰዱትን (ለግልጽነት እንዲረዳ ካደረግናቸው ጥቃቅን ለውጦች ጋር) አቋሞች በሙሉ ልባችን እንደግፋለን። ሌሎችም አካላት የተባለውን ሰነድ አጥንተው ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወስዱ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀረባለን።

1. የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ የህዝብን ፍትሃዊና ህጋዊ መብቶችና ጥያቄዎች ለማፈን ባለፉት 20 አመታት በተለያዩ የኣገሪቱ አካባቢዎች በተለይ ደግሞ በኦሮምያ፣ በኦጋዴን: በጋምቤላና በሌሎችም ክልሎች ህዝቦች ላይ የሚያካሄደውን ወታደራዊ የእመቃ ዘመቻ አሁኑኑ ያቁም።
2. በሃገሪቱ እስር ቤቶች የሚማቅቁ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አሁኑኑ ይፈቱ።የሰው ልጆች ቄራ የሆነውና የሰቆቃ ስራ መፈጸሚያ የሆነው የማእከላዊ እስርቤት ባስቸኳይ ፈረሶ ለዘላለሙ ይዘጋ
3. የአገዛዙ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማስተካካያ እስኪበጅለት ድረስ ይህ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ችግር ላይ ለጣላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ዳቦ፣ ስኳር: እህልና ዘይት የመሳሰሉት የመሰረታዊ ፍጆታ እቃዎች ባስቸኳይ ከመነሻው የመንግስት ድጎማ ተደርጎላቸው ለህብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚደርስበት መንገድ ይመቻች::
4. የመለስ ዜናዊና የቤተሰቡ ንብረት ባስቸኳይ እንዲወረስ፤ ልኩ በውል በማይታወቀው የመለስ ቤተስብና የቅርብ ባለሟሎቹ የሙስና ተግባራት የምርመራ ስራ አሁኑኑ ይጀመር ።
5. የኢትዮጵያን ህዝብ ለአለም አቀፍ ጌቶች ባሪያ የሚያደረገው መሬት ለባእዳን አሳልፎ የመሸጥ ፐሊሲ አሁኑኑ ይቁም። በዚህ ረገድ የተደረሱ አለም አቀፍ ውሎች በሙሉ አሁኑኑ ይሰረዙ።
6. መለስ ዜናዊ ባስቸኳይ ከጠቅላይ ሚስትርነቱ ይነሳ የመንግስትን ስልጣን ባስቸኳይ ይልቀቅ።
7. ህገ ወጥ በሆነና በተጭበረበረ ምርጫ የተቋቋሙት የህዝብ መወሰኛና የፌደራል ምክር ቤቶች አሁኑኑ ይፍረሱ። ሁሉም የነጻነት ንቅናቄዎችና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የተሳተፉበት ዓላማው ማህበራዊ ፍትህንና ዴሞክራሲን ማንገስ የሆነና በኣጭር ጊዜ በነጻ የምርጫ ተቋምና ኣለምኣቀፍ ታዛቢዎች ሙሉ ለሙሉ በተመሰከረለት ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ መንግስት የሚያቋቁም የሽግግር መንግስት ይቋቋም።

   ከነዚህ በላይ በኦሮሞ ወጣቶች ከቀረቡ ጥያቄዎች በተጨማሪ ንቅናቄያችን የሚከተሉትን ቁልፍ ነጥቦች የመታገያ አጀንዳዎቻችን ወስጥ እንድንጨምራቸው ጥሪ ያቀርባል።

8. በቅርቡ በነዳጅ ላይ የተደረገው የዜጎችን ህይወት ለከፋ የኢኮኖሚ ስቃይ የሚዳርገው የዋጋ ጭማሪ ባስቸኳይ እንዲነሳ
9. በኦፊሴል ያልታወጀው ግን በተግባር በስራ ላይ የዋለው የኣስቸኳይ ጊዜ ኣዋጅ ይነሳ:: በሃገሪቱ ህገ መንግስት የተደነገጉት የመናገር: የመጻፍ: የመሰብሰብ: ስላማዊ ስልፍ የማድረግ መብቶች ሙሉ በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አሁኑኑ እንዲከበሩ። እነዚህ መሰረታዊ የሰብአዊና የሲቪል መብቶችን ለመጣስ የተደነገጉ ህጎች በሙሉ፤ ባለፉት ጥቂት አመታት የወጡትን የጸረ ሽብር ህግ፤ የፕሬስ ህግና፤ የመያድ ህጎችን ጨምሮ እንዲሰረዙ።

የኢትዮጵያ ህዝብ የኣባይን ወንዝ የመገደብና በኣግባቡ መጠቀምን ጨምሮ፤ ኑሮውን ለማሻሻልና ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ያሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች ሁሉ በኣለም ኣቀፍ ህግ መሰረት የመጠቀም መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በትራንፎርሜሽን፤ በአባይ ግድብና በሌላም ግንባታ ስም ወያኔ የሚያደረገው ተራ ማጭበርበር ባስቸኳይ እንዲቆምና በዚህ ማጭበርበሪያ ስም ወያኔ/ኢህአዴግ ከህዝብ የሰበሰበውን ገንዘብ ለባለቤቶቹ ባስቸኳይ እንዲመልስ።

**ከዚህ በላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ጥያቄዎቹን የጋራ አድርገን በጋራ እንነሳ ።**

**ኣመሰግናለሁ::**

## ወያኔ ለካራቱሪ ኩባንያ ሰጥቶት የነበረውን ሰፊ መሬት የተወሰነውን ክፍል መልሶ መውሰዱ ታወቀ

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ካራቱሪ ለሚባለው የህንድ ኩባንያ በገፍ ከሰጠው መሬት ላይ ከ147 ሺ ሄክታር በላይ መልሶ እንደወሰደ ብሉምበርግ የተባለው ድህረ ገጽ ዘገበ። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ይህንን መሬት መልሶ ለመውሰድ የተገደደዉ ከአለማቀፍ ማህበረሰብ በደረሰበት ጫናና በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ለም የአገራችንን መሬት ለባዕዳን አሳልፎ መሰጠቱን ተቃውመው በሰፊው መንቀሳቀስ በመጀመራቸው ቢሆንም ዋናዉ ምክንያት ግን እንካችሁ ብሎ ለባዕዳን የሰጠዉ መሬት ባዕዳኑን ራሳቸዉን አስገርሞ ለትችት በማብቃቱ ነዉ፤ በተለይ የካራቱሪ ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ በቅርቡ ወደ ጋምቤላ ተጉዞ ስለመሬት ቅሚያ ጥናታዊ ፊልም ለሰራው ለጋርዲያን ጋዜጠኛ ያንን የሚያክል ለም መሬት በነጻ ማግኘቱ እንዳስገረመዉ በመናገሩና ፊልሙ በመላው አለም በመሰራጨቱ በአገዛዙ ዙሪያ ቅሬታ መፍጠሩ ለመሬቱ መመለስ ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ የወያኔን ገመና የሚያዉቁ የፖለቲካ ተንታኞች አስረግጠዉ ይናገራሉ።

በፊልሙ ላይ የኩባንያው ባለቤት "መሬቱን ሲሰጡን ሄደን አላየነውም ዝም ብለው ሰጡን ወሰድን" ብለዉ መናገራቸው በአንድ በኩል ህዝባዊ ቁጣዉን እንዳባባሰዉና በሌላ በኩል ደግሞ የገዢውን ፓርቲ ማንነት በግልጽ ማሳየቱ ይታወሳል። የኩባንያው ባለሀብቶች እንዲህ አይነት ንግግር ባይናገሩ ኖሮ ህንዳዊዉ ኩባንያ ካራቱሪ ጭራሽ ተጨማሪ መሬት ያገኝ እንደሆነ እንጂ ወያኔማ የኢትዮጵያ ጉዳይ የማይጨንቀዉ ጉድ መሆኑን ከብዙ የህዝብ አስተያየት መረዳት ተችሏል።

የካራቱሪው ዋና ስራ አስኪያጅ ሳይ ራማካሪሻና ካራቱሪ ለብሉምበርግ እንደገለጹት ዜናው ፈጽሞ መሰረት የሌለው ነው ከማለት ውጪ የአንድ አነስተኛ የአውሮፓ አገርን የሚያክል መሬት ያገኘው ካራቱሬ መሬቱን ስለመቀማቱ የገለጸው ነገር የለም። ለካራቱሪ የተሰጠው መሬት በአለም ላይ በርካሽነቱ ተወዳዳሪ የሌለው ሲሆን፣ ኩባንያው በአመት ለአንድ ሄክታር መሬት የሚከፍለዉ አንድ የአሜሪካን ዶላር ብቻ ነዉ ። የሚገርመዉ ዘረኛዉ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አስከዛሬ የሰጠዉ መሬት አልበቃ ብሎት አሁንም ለተለያዩ አለማቀፍ ኩባንያዎች የእርሻ መሬቶችን በርካሽ ዋጋ በመቸብቸብ ላይ ነዉ።

ከዚሁ ጋር በተያየዘ ከፍተኛ መጠን ያለው የአገሪቱ የደን ኃብት ሊተካ በማይችል ሁኔታ መውደሙ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከቀያቸው እንዲፈናቀሉ መደረጉና፣ አርብቶ አደሮች ለከብቶቻቸው የሚሆን የግጦሽ ቦታ አጥተው መቸገራቸው በተደጋጋሚ መዘገቡ ይታወሳል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ወያኔ ህዝባችንን እያፈናቀለ ለውጪ ባለሃብቶች እንደገና ዳቦ የሚያከፋፍለው መሬት በአስቸኳይ እንዲቆም ከመጠየቅ አልፎ ኢትዮጵያ የራሷን ጥቅም የሚያስጠብቅላት መንግሥት በምትመሰርትበት ጊዜ አሁን በዘረፋው በመተባበርር መሬታችንን እየወሰዱ ያሉ ሁሉ ምንም አይነት ህጋዊ ዋስትና እንደማይኖራቸው ልያውቁት ይገባል ሲል ማስጠንቀቁ ይታወቃል።

## በውጪ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በቶሮንቶ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የህብረትና የአንድነት መንፈስ ወደፊትም መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል። በመጨረሻም ይህ ዛፍ መርዘኛ ስለሆነና እህሎቹን ስላቀጨጫቸው ከስሩ ለመንቀልና በአገራችን ፍትህና ርትእ ለማስፈን አብረን መስራት ይኖርብናል በማለት ማሳሰባቸውን ተገልጿል።

ሁለተኛዉ ተናጋሪ የኦጋዴን ማህበረሰብ ተወካይ የሆኑት አቶ መህመድ ሀሰን ደግሞ፡ "እድሜ ልካችንን በማይረቡ ነገሮች እየተጨቃጨቅን ከመኖርና፡ በቋንቋና በሀይማኖት ዙሪያ ተሰባስበን ከምንለያይ የአላማና የትግል አንድነት ፈጥረን፡ አገራችንን እያጠፋ ያለውን ስርአት ማስወገድ አለብን ማለታቸውን ዘጋቢያችን አያይዞ ገልጿል። አቶ መሃመድ በመቀጠልም ሕወሀት/ኢህአዴግ ላለፉት አመታት በተለይም በኦጋዴን አካባቢ ከፍተኛ የሆነ እልቂት ሲፈጽም ገና ለገና ተገንጣይ ቡድኖች ናቸው ብሎ በማሰብና በመፍራት፡ በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ በኦጋዴን የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ተቃውመን በአንድነት አለመውጣታችን እጅግ እንደጎዳን ገልጸዋለ፡ አሁንም ወያኔ ለምእራባዊያን የሚሸጠውን የፈጠራ ፖለቲካ ተባብረን ካልደመሰስነው በስተቀር፡ እርስ በርሳችን ስንባላ ያቺ የምንወዳት አገር ልትጠፋ እንደምንችል አሳስበው የጋራ ዓላማ ይዘን ልንቀሳቀስ ይገባል ሲሉ ጥሪ ማቅረባቸዉን ዘጋቢያችን ገልጿል።

ሶስተኛ ተናጋሪ የሆኑት አቶ አበበ በለውም፡ አሁን የስራ ጊዜ ነው፡ ጠላቶቻችን እያንዳንዱን ሰዓት ለአፈናም ይሁን ለዝርፊያ በስራ ነዉ የሚያሳልፉት፡ እኛ ግን እስካሁን ወሬ ከማዉራት ፈቀቅ እንዳላልን ገልጸው፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የአንዱ ብሄር ችግር የዚያ ብሄር ብቻ ሳይሆን የሁሉም ኢትዮጵያዊ ችግር ስለሆነ ችግራችንን ለማስወገድ ተባብረን መስራት እንዳለብን አሳስበዋል። አራተኛው ተናጋሪ ነበሩት ወጣት ጃዋር መሐመድ ደግሞ በበኩላቸዉ ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲን ለማስፈንና፡ የመፈረካከስ አደጋን ለማቆም ህዝቡና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ማድረግ ስለሚገባቸው ነገሮች በዝርዝር መናገሩን የግንቦት 7 ዘጋቢ አክሎ ገልጿል። ወጣት ጃዋር፡ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ህዝቡን ቀድመው በመሄድ የማስተባበር ስራ መስራት እንዳለባቸዉ ካሳሰበ በኋላ የፖለቲካ ድርጅቶች ደጋፊ እናጣለን በሚል ፍራቻ ብቻ ተፈራርተውና ተራርቀው ከሚኖሩ ፡ ተጠጋግተዉ በመተማመንና በመተባበር በመስራት፡ የአንድነትና የነጻነት አራማጆችን፡ ወደመሀል አምጥተዉ አብሮ የመሄድ ባህል ማዳበር እንደሚገባቸዉ በጥብቅ አሳስቧል።

በመጨረሻም አቶ አባንግ ሜቶ ከራሱ ልምድና ከአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር ሰፊ ማብራሪያ አሰምቶ፡ ሁላችንም ነጻ ካልወጣን አንዳችንም ነጻ እንደማንወጣና፡ ከብሄር ግኑኝነት በፊት ሰብዓዊነት መቅደም እንዳለበት አሳስቦ የአብሮ መስራትን አስፈላጊነት አበክሮ ከገለጸ በኋላ ጠላታችን ይሄ ብሄር ወይንም ያኛው ብሄር ሳይሆን፡ የመለስ ዜናዊ ስርአት እንደሆነ ገልጾ፡ ይህንን ስርአት ለመጣል በጋራ እንድንታገል አደራ ማለቱን ዘጋቢያችን ጠቅሷል።

"አንድነት ሀይል ነው" በሚል መፈክር የተጀመረው የእለቱ ስብሰባ፡ አምስቱም ተናጋሪዎች በጋራ ባወጡት "አንድነት ሀይል ነው" እንዲሁም መለያየት በቃ በሚል መግለጫ መጠናቀቁ ታውቋል።

## በአማራ ክልል የሚገኙ ገበሬዎች የማዳበሪያ ዋጋ ስለተወደደባቸው ላለመግዛት መማማላቸው ታወቀ

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን በተደጋጋሚ እንደዘገበው በአማራ ክልል የሚገኙ አርሶ አደሮች አምና በ900 ብር ይሸጥ የነበረው አንድ ኩንታል ማዳባሪያ በአንድ ጊዜ አንድ ሺ 200 ብር በመግባቱ ዋጋው እስካልተስተካከለ ድረስ ምንም አይነት ማዳበሪያ ላለመግዛት መወሰናቸውንና ይህንን ውሳኔ የሚጥስ እንዳይኖር በየቤተክርስቲያኑ መማማላቸው ታውቋል። ከእሳት ዘጋባ መረዳት እንደተቻለዉ አርሶ አደሮቹ ይህንን እርምጃ ለመዉሰድ የበቁት በማዳበሪያዉ ዋጋ መናር ብቻ ሳይሆን በየአመቱ ለምርት የሚጠቀሙበት የምርጥ ዘር ዋጋ በአንዴ በማሻቀብ የአንድ ኩንታል ምርጥ ዘር ዋጋ ከ2 ሺ 500 ብር በላይ በማሻቀቡ ነዉ።

ኢትዮጵያ ወስጥ በየግዜዉ እያዘቀዘቀ በመጣዉ የኑሮ ውድነት ክፉኛ ከተጎዱት የህብረተሰብ ክፍሎች አንዱ ገበሬዉ ሲሆን ይህ አሁን የታየው የማዳበሪያ እና የምርጥ ዘር ዋጋ ንረት በመጪው የግብርና ምርት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽኖ ከመፍጠሩ ሌላ ገበሬዉንም ሆነ ሌላዉን ሸምቶ አዳሪ ህዝብ ከፍተኛ ችግር ዉስጥ እንደሚከተዉ ብዙዎች በአጽንዖት ይናገራሉ። እነዚህ በዋጋ ንረት የተማረሩት ገበሬዎች ወያኔ በአስቸኳይ ልዩ ድጎማ አድርጎ የማዳበሪያና የምርጥ ዘር ዋጋን ካላረጋጋ፣ የጀመሩትን አድማ እንደማያቆሙ ገልጸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ዉስጥ ማዳበሪያ በማስመጣትና በማከፋፋል ስራ ላይ የተሰማራው አምባሰል የተባለው የወያኔ ኩባንያ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ምንም አይነት የሂሳብ ምርመራ የማያውቀው ድርጅት እንደሆነና አስከዛሬ ሂሳቡን ኦዲት አስደርጎ እንደማያውቅ ይታወቃል።

ከዚሁ ከዋጋ ጋር በተያያዘ ዜና አዲስ አበባ ቃሊቲ ዉስጥ የሚገኘው እስር ቤት ከዋጋ ጭማሪ ከቫትና ከካሽ ሪጂስትር ጋር በተያያዘ በሚታሰሩ ነጋዴዎች በመጨናነቁ ቁጥራቸዉ በዛ ያለ ነጋዴዎች ወደ ሸዋ ሮቢት እስር ቤት በግዴታ እየተዛወሩ መሆናቸው ታውቆአል።የኢሳት ዘጋቢ የእስር ቤቶችን ምንጮች ጠቅሶ እንደዘገበው ቫት አጭበርብራችሁዋል በሚል የሚታሰሩ ነጋዴዎች ቁጥር መጨመር በአገሪቱ ውስጥ የእቃዎችን እጥረትና የዋጋ ውድነቱን አባብሶታል ተብሎአል።

በቅርቡ የዋጋ ግሽበትን እንቆጣጠራለን በሚል ሰበብ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ያወጀዉ የዋጋ ቁጥጥር ዘይትና ሌሎችም መሠረታዊ ሸቀጦች አገሪቱ ሙሉ እንዲጠፉ ምክንያት በመሆኑ ወያኔ እንደቀድሞው የመንግሥቱ ሃይለማሪያም ዘመን በቀበሌ አማካይነት በየወሩ አንድ አንድ ሊትር ዘይት በነፍስ ወከፍ ማከፋፋል ጀምሯል። በወር አንድ ሊትር ዘይት እንኳን አራትና አምስት ልጅ ያለበትን ቤተሰብ ወንደላጤዉንም ሳምንት እንደማያቆየዉ እየታወቀ ይህ ወያኔ የጀመረዉ የዘይት ቸርቻሮ ዘመቻ ስህተትን በስህተት ለማረም የሚደርግ አጉል ሩጫ እንጂ ሸማቹን ህብረተሰብ እንደማይጠቅም ህዝቡ ካወቀዉ ቆይቷል። ከአዲስ አበባና ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በተደጋጋሚ እንደሚሰማዉ አገሪቱ ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ መውጣቷ በገሀድ ይታያል። "ህዝቡ ምን በልቼ ልደር በሚል ሀሳብ በመጠመዱ ምንም ነገር ለማሰብና ለማሰላሰል ተስኖታል" ሲሉ ህዝቡ ያለበትን የኑሮ ሁኔታ ገልጸዋል።

## አዲስ አበባ ከተማ በትራንስፖርት እጥረት እየተጨናነቀች ነው፣ ነዋሪዎች ዘረኛው . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አዲስ የተፈጠረውን የታክሲ ችግር አስመልክቶ አስተያየታቸውን እንዲሰጡት ዘጋቢያችን ያናገራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች፣ ተመሳሳይ በሆነ አገላለጽ የአሁኑ የታክሲ ችግር ነጠላ ዜማ ደግሞ አዲስና ህብረተሰቡም ስለሌላ ነገር እንዳያስብ ማጥመጃ እንደሆነ እንደሚያምኑ ገልጸዋል። አስተያየት ሰጪዎቹ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በቅርብ ጊዜ የነጋዴውን ማህበረሰብ ከህዝቡ ጋር የማጣላት ሰፊ ዘመቻ ከፍቶ ሊሳካለት ባለመቻሉ አሁን ደግሞ ታክሲ አሽከርካሪና የታክሲ ባለሃብቶችን ከህብረተሰቡ ጋር በማናቆር በጋራ እንዳይቆሙ ለማድረግ የተጠነሰሰ ሴራ ነው ብለዋል። አያይዘውም በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ አመጽ ሊነሳ ይችላል የሚል ስጋት ያየለበት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እያንዳንዱአን ቀዳዳ ለማድፈን ሌት ተቀን እየሰራ እንደሆነ ገልጸዋል። በመጨረሻም ምንም አይነት አፈና ያድርግ ምንም አይነት ዘዴን ይቀይስ ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ አብዮት መፈንዳቱ ፍጹም አይቀሬ እንደሆነ በርካታ ምልክቶች እየታዩ መሆናቸውን በመግለጽ አስተያየታቸን አጠቃለዋል።

## በኢንቨስትሜንት ስም የሚካሄደው የደን ጭፍጨፋ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በቤነሻንጉል እና በኦሮሚያ አስከቅርብ ጊዜ የተቸበቸበው መሬት ሰው ያልሰፈረበት ነው በማለት ሽንጣቸውን ገትረው ይከራከሩ የነበሩ ለወያኔ ያደሩ ባንዳዎች ፤ ከመሬቱ ጥበት የተነሳ በተራራ ላይ ተንጠልጥሎ ከሚኖረው የመንዝ ህዝብ ላይ ስለተቀማው ሰፊ ቦታ ልማትን በክልሉ ለማስፋፋት ነው የሚል ሽፋን እየሰጡት እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል። ካራቱሬ እየተበለ የሚጠራው የህንድ ኩባንያ ዋና ሥራአስኪያጅ ስለመሬት ቅርምት ዶክሜንታሪ ፊልም ላዘጋጀ የውጪ ጋዜጠኛ፤ ኩባንያው እራሱ ማመን እስኪያቅተው ድረስ እዚህ ግባ በማይባል ዋጋ "ኑና ውሰዱ ተብሎ በለጋስነት የተሰጠን ቦታ ነው " በማለት በደስታ እየፈነደቀ ምስክርነት ሲሰጥ ተዘግቦ ለአለም ተሰራጭቶአል።

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢንቨስትመንት ስም የውጭ አገር ባለሀብቶች የእርሻ መሬት ለመቀራመት ወደ ኢትዮጵያ እንዲጎርፉ ማድረጉን ተከትሎ የአገሪቱ የደን ሀብት በከፍተኛ ደረጃ መራቆቱ በርካታ ብርቅየ የዱር እንስሳትም ሊተኩ በማይችሉበት ሁኔታ እየወደሙ አካባቢውም ወደ ምድረ በዳነት እየተቀየረ መሆኑን በርካታ የአካባቢ ተቆርቋሪዎች እያሳሰቡ መሆኑ በስፋት ይታወቃል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።


**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org